**በዳዊት ተመስገን**
**ኦስሎ ኖርዌይ**

*የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከአምባገነኑና ዘረኛው መለስ ጠቅላይነት እስከ ራዕይ አስፈፃሚው ኃይለማርያም ደሳለኝ!!*

*ከጥቂት ዓመታት በፊት አቶ መለስ ይጠቀሙበት የነበረች አንድ ብሂል ነበረቻቸው "አፍሪካ ስማቸው" በ "M" የሚጀምር ሁለት አምባገነኖች አይታለች ፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም እና ሞብቱ ሴሴኮ፡፡ በእነርሱ ላይ ሶስተኛ "M" መጨመር አልፈልግም ይሉ ነበር ነገር ግን እርሳቸው እራሳቸው የአምባገነኖች አለቃ ሆነው ነበር የከረሙት በጊዜ ርዝመትም ከፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም ይበልጣሉ፡፡*
*በህወሓት የመሪዎች ስብሰባ ውስጥ የትግል ዘመን እኩዮቻቸውም ሆኑ በ1993ቱ የመሪዎቹ ትንቅንቅ እርሳቸው አሸናፊ ሆነው እንዲወጡ የረዷቸው አሁን ከውጭ ሆነው የኢትዮጵያ ህዝብን በዝባዥ ስብሃት ነጋ ሥልጣን ላይ የሉም፡፡ አቶ መለስ እንደደረሱበት ሥልጣንን የመጠቅለል ጥግ ፋሽስቱ መንግሥቱም በስርዓታቸው ዘመን ማምሻ ወቅት ደርሰውበት እንደነበር ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ* “The Burden of history” *በሚለው ብዕራቸው ጽፈዋል፡፡*

*የኢትዮጵያ የአምባገነንነት የፖለቲካ ባህል ከሀገሪቱ የፖለቲካ ተሞክሮ እንደሚነሳ የሚናገሩት ፕሮፌሰሩ ሁኔታውን "የታሪክ ሸክም" ሲሉ ጠርተውታል፡፡ ጊዜው* 1990 */እ.ኤ.አ* 1997 */ ወቅት ነው ቦታው የአፍሪካ ኮሚሽን አዳራሽ ሲሆን በአዳራሹ ውስጥ የሀገሪቱ ዋነኛ የፖሊሲ ጉዳዮች የሚወስኑ እና የሚያስወስኑ የህወሓት ገዳይና አስገዳይ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በሙሉ ተገኝተዋል፡፡በዚህ ስብሰባ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ምን ሊሉ እንደመጡ ብዙዎች አልገመቱም ነበር፡፡ እናም አቶ መለስ ግን እንዲህ በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ "በሀገሪቱ የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ የህወሓት የበላይነት አብቅቷል” ሰውየው እንዲህ ለማለት የበቁት ሁለት አከራካሪ ምክንያቶችን ይዘው በመቅረብ እንደሆነ ፕሮፌሰር ጳውሎስ ሚልኪያስ* “Ethiopia, TPLF and Roots of the 2001 Political Tremor:" *በሚል ስራቸው ያትታሉ እንደ አቶ መለስ አጭበርባሪነት እና ውሸታምነት ክርክር የመጀመሪያው ምክንያት ፓርቲው የታገለለትን የትግራይንም ሆነ የሌሎችን የሀገሪቱን ዜጐች* (Ethnics) *ጥያቄ መልሷል፡፡*

*ከኢዲዮ፣ ኢህአፓ፣ የደርግ እርሳቸው "ጠባብ ብሔርተኛ" ብለው እስከሰየሙት ኦነግ ድረስ ያሉት ከሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት መወገዳቸው እና የትኞቹም ክልሎች የመገንጠል መብት ማግኘታቸው ህወሓት ሕልሙን እንዳሳካ ተነተኑ፡፡ማንኛውም ህብረተሰብ ልብ እንዲለው ወይም እንዲገነዘበው የምለው ነገር ቢኖር ስለ ብሔረሰቦች ጥያቄ ማለት የራስን እድል በራስ መወሰን ብሎም እስከ መገንጠል የሚለውን መርህ ያወጣው ወያኔና ሻዕብያ እንደሆኑ ማንኛውም ህብረተሰብ እንዲያውቀው እገልፃለሁ። ኢሕአፓ እንዳልሆነ ማንኛውም ህብረተሰብግልፅ እንዲሆንላችሁ በዚሁ አጋጣሚ አሳስባለሁ።*

*እኔ እስከማውቀው የታወቁት የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ተመራማሪ/አርኪዎሎጂስት/ ፕሮፌሰር ዣንዶሬሰም ስለ ኢትዮጵያውያን የጻፉት፡፡ “የኢትዮጵያ ሕዝብ በስራ የሚያምን ከሌላው የአፍሪካ ሕዝቦች የሚለየው የሃይማኖት፣ የጎሣ፣ የቀበሌ ልዩነት ትርጉም ስለማይሰጠውና ኢትዮጵያዊነት ሁሉንም ስለሚያስተሳስረው ነው፡፡ በዘመነ መሳፍንት ጊዜ እንኳ ሕዝቡ ለተለያዩ ገዥዎች ቢገብርም በኢትዮጵያዊነቱ ላይ አንዳችም እንከን አልገባም ሕዝቡ በሃይማኖትና በጎሣ የማይከፋፈል ጠንካራ ሕዝብ ነው፡፡” ይላሉ፡፡*

እውነት ብለዋል ፕሮፌሰሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንድነቱ እና ለኢትዮጵያዊነቱ አሁንም የቆመ ነው፡፡ የተደነቁት አሜሪካዊ ምሁርና ዲፕሎማት ዲን ኦኪሰን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ስለ አሜሪካ የፖለቲካ አቅጣጫ ባቀረቡት መጽሐፍ ላይ እንደሚሉት የፖለቲካ ድርጅቶች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የአንድ ዓይነት ክስተት አዋላጆች (Midwives of history) ይሆናሉ ይላሉ፡፡

ከዚህ ስንነሳ ኢሠፓአኮ የኢሠፓ አዋላጅ ነበር፡፡ አሁንም በወያኔ ፊውታራሪነት የተቋቋመው "የሽግግር መንግሥትም" ሰኔ 24 ቀን 1983 በተካሄደው ኮንፈረንስ የተሰጠው የታሪክ አዋላጅነት ሚና በቻርተር አንቀጽ ሁለት ላይ ቁልጭ ብሎ የተቀመጠው ነበር፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነቱንና ሉአላዊነቱን ለመከፋፈል ይኸውም ሁሌ ወያኔ እንደ ተረት የሚደግመው ይህ ሃሳብ "የራስን ዕድል በራስ መወሰን" የሚለው የፖለቲካ ጽንሰ ሃሳብ ከሟቹ የሶቭዬት ኅብረት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17 እና 18 የተወሰደና በብዙ የበሰሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች አመለካከት ይህ "የማረክሲስት ሌኒኒስት" ፍልስፍና ሲያስፈልግ አገሮችን ያለነገሩ የሚያስተሳስር /እንደ ቀድሞዋ ሶቬዬት ኅብረት/ ሲያስፈልግ ደግሞ ሕዝቡንና አገርን የሚበታትን ነው፡፡ ጆን ስፔንሰር እንደሚሉት ይህ ፍልስፍና ለተንኮል አርአያነቱ የማኪያቬሊን የከፋፍሎ መግዛት ትምህርት የተካኑት የሌኒንና የስታሊን ፍልስፍና ነው፡፡

"የራስን ዕድል በራስ መወሰን" ፕሮፌሰር ባሪ ሩቢ "ሞደርን ዲክታተርስ" በሚለው መጽሐፋቸው "የአገርና የሕዝብ አንድነት መበታተኛ ፍልስፍና ይሉታል "፡፡ጠ/ሚኒስትሩ በሁለተኛነት ያቀረቡት ምክንያት ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በተከተሉት ዓመታት ከሶሻሊስታዊ ራዕዩ የመራቅ የሙስና እና የአምባገነንነት ችግሮች በፓርቲው ውስጥ መታየታቸው እንደሆነ ተናገሩ፡፡ እርሳቸው ለዚህም መፍትሄ ብለው ያቀረቡት ህወሓትን ጨምሮ እና በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የትኞቹም የፖለቲካ ስብስቦች ርዕዮተ ዓለም ላይ ተደራጅተው እንዲፎካከሩ ማድረግ ነው ሲሉ በካናዳ የሚገኙት የወግ አጥባቂ ሊበራል ኮሚኒስት አልፎም የኩቤክን መገንጠል የሚደግፉትን ፓርቲዎች በምሳሌነት ጠቅሰው የትግል ጓዶቻቸውን ሞገቱ።

አቶ መለስ ህወሓትን የመበተን ሀሳባቸውን ያመጡት የርዕዮት ዓለም መሸጋሸግ አድርገው ሳይሆን የሀገሪቱን ሥልጣን ጠቅልለው መያዝ እንዳይችሉ የተገዳደሯቸውን ጓዶቻቸውን አስቀድሞ ለመምታት የታለመ ሃሳብ እንደነበር ፕሮፌሰር ጳውሎስ ይጠቅሳሉ፡፡ እንደ ፕሮፌሰሩ አስተያየት መቀሌ የከተመው የፓርቲው ላዕላይ መዋቅር እርሳቸው የማይስማሙባቸውን አንዳንድ ውሳኔዎች እያሳለፉ ለውሳኔዎቹ ተገዢ እንዲሆኑ መደረጋቸው ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም ሲጠቅሱ ማዕከላዊው መንግሥት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንን ጨምሮ ሌሎችንም ተቋማት ወደግል የማዛወር ሃሳብ ቢኖረውም ይሄ ግን በፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ በኩል ድጋፍ ባለ ማግኘቱ ተቋማቱ ወደግል እንዲዛወሩ እንደተደረገ ያነሳሉ፡፡

በዚህ ስብሰባ ላይ የታየው የአቶ መለስ አቋም ፋሽስቱ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን " ለምሳ ሲያስቡት ለቁርስ አደረግናቸው የሚለውን ብሂል ያስታውሰኛል " ሲሉ ፕሮፌሰር ጳውሎስ ከላይ በጠቀስነው ጽሑፋቸው ይገልጻሉ፡፡አሁንም ቢሆን ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያራመዱ ያሉት በጠባብ ዘር ብሔርተኝነት ላይ  የተመሰረተ ነው እየሰሩ ያሉት ስለ ኢትዮጵያ የአንድነት ጥያቄ አይደለም።

አንጋፋውና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፊር ቀዳጅ  ከዛሬ 40 ዓመት በፊት ኢሕአፓ የጠየቀው ጥያቄ አለ ኢሕአፓ ራሱን ለሕዝብ ሲያስተዋውቅ ከሚታገልላቸው ዋና ዋና መርሆዎቹ ውስጥ "በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለ ገደብ እንዲከበሩ የመንግስት ስልጣን ከሕዝብ እንዲመነጭ መሬት ላራሹ በጾታና በእምነት ልዩነት እንዳይኖር፣የአገሪቱ ሉዓላዊነት እንዲከበር፣ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገውና በነፃ ተዘዋውሮ መስራት እንዲችል።"

የመሳሰሉት የሚገኙበት ነበር ነገር ግን እስከዛሬ ድረስ አንዱ እንኳን አልተመለሰም።ፕሮፌሰር ነን ባዮች ወይም የታሪክ ተመራማሪ ነን የሚሉትም አሁንም ቢሆን በወያኔ ጉያ ውስጥ ሆነው ለእውነት ሳይቆሙ እድሜ ልካቸውን እንደ ውሃ ላይ ኩበት ሲንሳፈፉ እያየናቸው ነው።
"ባህላችን የአገዛዝ ነው!"

የፖለቲካ ባህል የሚለው ሃገር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ፖለቲካ ሳይንሱ መዝገበ ቃላት የገባው እ.ኤ.አ በ1950ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ በአሜሪካ ከተጀመረው የቢሄቨራል ፖለቲካ ሳይንስ በኩል ነው፡፡ በዚህ አስተምህሮት መሰረት የአንድ ማህበረሰብ የፖለቲካ ባህል የሚለው ማህበረሰቡ የሀገሪቱ የፖለቲካ ስርዓት እንዴት እንደሚከወን ያለውን ሀገራዊ ቅሬታ የሚያስተናግዱበት መንገድ ግለሰቦችም ሆኑ ሌሎች የማህበረሰቡ ክፍሎች ፖለቲካዊ ፍላጐቶቻቸውን ለመፈጸም ያላቸውን እድል የሚይዝ ሲሆን ከእነዚህ ክስተቶች መስተጋብር በኋላ የሚፈጠሩ እሴቶች እና የመልካም እና የክፉ ድርጊት መመዘኛ የሚሆኑት የማህበረሰብ ልማዶች የሀገሬውን የፖለቲካ ባህል ይወስናሉ፡፡ ይህን መሰሉ ባህል በታሪክ፣ በኢኮኖሚ ተሞክሮ እና በኃይማኖት ተጽዕኖ ስር ቢያርፍም አብዮት መሰል ሁኔቶች እስካልተከሰቱ ድረስ ከትውልድ ወደ ትውልድ የመሸጋገር እድሉ የሰፋ ነው፡፡ ይህም ማለት አንዱ ትውልድ የሀገሬውን ፖለቲካ የሚወስኑትን ዋነኞቹን የፖለቲካ ባህሉ መገለጫዎች የሚወርሰው ከቀደመው ትውልድ ይሆናል፡፡

በፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን እምነት እነዚህን የፖለቲካ ባህል መገለጫዎችን ማጥናት የሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ምን ያህል ለዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች ምቹ የመሆንና ያለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ሉሲያን ፒዮ የአንድ ሀገር ፖለቲካዊ ባህል እርስ በእርስ በመሪዎች ላይ ጥርጣሬ በሚኖር ጭፍን እምነትና ባለሥልጣናትን ባለመተቸት ፍርሃት ከተበከለ አምባገነናዊ አገዛዝን ለመሸከምም ሆነ ለመፍጠር ምቹ መሰረት ይሆናል ሲሉ “Asian Power and Politics” በሚለው መጽሐፋቸው ይናገራሉ፡፡እንደ እርሳቸው በእራስ የመተማመን መንፈስ በእርስ በእርስ ግንኙነት ላይ የሚኖር እምነት እና በአገልጋይነት መንፈስ ያልተበከለ የመሪዎች እና የተመሪዎች ግንኙነት መሰል እሴቶች ያሉት የፖለቲካ ባህል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ብዙም አይቸግርም፡፡የኢትዮጵያን የፖለቲካ ባህል በተመለከተ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ የፖለቲካ ተንታኞች ተቀራራቢ አቋም ያንፀባርቃሉ የ1997ቱን ምርጫ ተከትሎ በተቋሚዎችና በገዥው ፓርቲ የተወሰዱትን አቋሞች እና የሀገሪቱን የበረዶ ያህል የዴሞክራሲ ቅዝቃዜ ያጠኑት ሆላንዳዊው ጆን አቢቢኒክ የሀገሪቷን የፖለቲካ ባህል ምርጫውን ተከትሎ ለመጣው ክስተት ተጠያቂ ያደርጋሉ፡፡ እንደ እርሳቸው ክርክር “የእጦት ኢኮኖሚክስ” (Economics of Scarcity”) የኢትዮጵያን የፖለቲካ ባህል በሚገባ ይገልጻል፡፡

በዚህ አረዳድ መሠረት በፖለቲካው ጨዋታ አሸናፊ ሆኖ የሚወጣው የፖለቲካ ልሂቅ የሀገሪቱን ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጮች ይቆጣጠራል፡፡ ከዚህ የኢኮኖሚ አውታሮች ከሚያገኛቸው ጥቅሞች በመንተራስ ወያኔ ለእርሱ ብቻ የሚታዘዙ ሰዎችን በስሩ ይሰበስባል፡፡ በዚህ ሂደትም ሥልጣን መዋቅራዊ ከመሆን ይልቅ የመሪውን ባህሪ ይለብሳል፡፡ ለዚህም ነው ይላሉ ፕሮፌሰር ጆን “Discomfiture of Democracy: በሚለው ሥራቸው "አመጽ በተቀላቀለበት የሀገሪቱ የፖለቲካ ባህል ውስጥ የፖለቲካ ትግል የሞት እና የሽረት ጉዳይ ሆኖ የሚታየው" ማለት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የወያኔ አመጽ ማንሳት በአጠቃላይ የፖለቲካ ባህል አሳጥቶታል የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ፍትህ ነፃነት አለመኖር ከማዕከላዊው መንግሥት ባህርይ ይነሳል፡፡

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ መንግሥቱን መያዝ የሀብት እና የታላቅነት መነሻ ሆኖ መኖሩ ገዢ ልሂቃን ነኝ ባዮች ለሰላማዊ ወይም ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ዝግጁ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ራሱን ከማዕከላዊው መንግሥት ተጽዕኖ ያላቀቀ መሠረተ

ጠንካራ የሆነ መካከለኛ መደብ ያለመኖሩ ማዕከላዊው መንግሥት ብቸኛ የሀብት ምንጭ ለመሆን እንደተዳረገ ፕሮፌሰር መስፍን "A Review of the Addis Ababa May 1993 Constitution Symposium" በሚለው ጽሑፋቸው ይገልጻሉ፡፡

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ፖለቲካ ጅማሮ እንደሆነ ከሚታመነው ከ1960ዎቹ ጅማሮ የተነሱት የሀገሪቱ የፖለቲካ ስብስቦች ከግራ ዘመምነታቸው ባህሪ ጋር ተዳምሮ ይህን የማዕከላዊ መንግሥት የፖለቲካ ባህል መረዳታቸው ይህንኑ ባህል ከማጠናከር ውጪ ሌላ እሴት እንዳያስተዋውቁ ገቷቸዋል፡፡እነዚህ የፖለቲካ ስብስቦች ምንም ያህል ዘመናዊ ፖለቲካን ወደ ሀገሪቱ የፖለቲካ ተዋጽኦ ለማምጣት እና ከዚህ በሚነሱት ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች ሀገሪቱን ለማዋቀር ቢሞክርም የትውልድ የፖለቲካ ባህል ከቀደመው ትውልድ ጋር ብዙም የተለያየ እንዳልነበር ዶ/ር አሰፋ እንዳሻው "Ethiopia Perspectives for change and renewal" በሚለው ሥራቸው ይከራከራሉ፡፡ እንደ ኦክስፎርድ መምህር ሙግት ኢትዮጵያውያኑ ስር ነቀልተኛ አብዮተኞች ከአገሪቱ ልማዳዊው የመሪ ሁለንተኘነት እና የተመሪዎች ምንምነት የፖለቲካ ተለምዶ እንዳልተላቀቁ ይናገራሉ፡፡ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ አረዳድ መሪ ከሕይወት የገዘፈ እና ሁሉን ማድረግ የሚችል (Herculean) ሲሆን መሪዎች በበኩላቸው ለመሪዎቻቸው ግለ አምልኮትን ከማልበስ ውጪ አንዳችም አበርክቶት እንደማይኖራቸው መታመኑ የሀገሪቱ የፖለቲካ ባህል ለአንድ ብቸኛ አምባገነን ለወያኔ መንግሥት የተመቸ አድርጎለታል ሲሉ ይሞግታሉ፡፡

ከዚህ ዘመን ትውልድ ጋር በተዛማጅነት ጅማሮውን ያገኘው የሀገሪቱን የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ አወቃቀርም ለአምባገነናዊ የፖለቲካ ባህል ሌላው ተጠቃሽ ምክኒያት ነው።የአፍሪካን ዘመናዊ የፖለቲካ በፓርቲዎች በጥልቀት ያጠኑት ፕሮፌሰር መሐመድ ሳሊህ የአፍሪካን የዲሞክራሲ የኋልዮሽ ጉዞ ከዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ አደረጃጀት ጋር ያያይዙታል፡፡ "እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይላሉ መሐመድ ሳሊህ "African democracies and African Politics" በሚለው መጽሐፋቸው ፖለቲካዊ መሀይምነት በተጠናወታቸው አባላት መመስረታቸው ፓርቲዎቹን ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን እንዳያበረታቱ ገቷቸዋል፡፡ ይህን መሰል ፓርቲዎች ደግሞ ከፓርቲዎቻቸው ደጋፊዎቻቸውም ሆነ አባላት ተጠያቂነት ውጪ ውሳኔዎችን የመወሰን እድል ስለሚኖራቸው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባህል ግድ የሚለውን ተጠያቂነትን መሠረት የሚያደርገውን የመሪ እና የተመሪዎችን ግንኙነት እንዳይሰምር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም እንደ ገዥው የወያኔ መንግሥት ያሉ ዘውግን ማዕከል የሚያደርጉ (Ethnic Oriented) ፓርቲዎች መሪዎቻቸውን የሚመርጡበት መንገድ እጅግ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እንደሆነ ፕሮፌሰር መሐመድ ይከራከራሉ፡፡

እንደ ሱዳናዊው የፖለቲካ ሳይንስ መምህር ዘውግ ተኮር ፓርቲዎች መሪዎቻቸውን የሚመርጡት በችሎታ (Merit) ሳይሆን ቀድሞ በሚታወቅ ውሳኔ መሆኑ ፓርቲዎቹ ሀገራቸውንም ሲያስተዳድሩ ከዚህ ባህል ለመላቀቅ ስለሚከብዳቸው የየፓርቲዎቹ መሪዎች ወደ አምባገነንነት እንደሚያዘነብሉ ይናገራሉ፡፡ሀገራችን ሦስት ተከታታይ ሥርዓታት ጋር በአደባባይ ሲነታረኩ ለከረሙት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም የሀገሪቱ ቁልቁል የፖለቲካ ጉዞ መነሻ ፖለቲካዊ ባህላችን ስለመሆኑ ላለፉት ሃያ ዓመታት ሲከራከሩ ቆይተዋል፡፡ እንደ ፕሮፌሰር ጆን አቢቢኒክ ከላይ በጠቀስነው ሥራቸው የወያኔ አምባገነንት ታሪክ ከዛጉዌ ሥርወ መንግሥት የሚነሳ ታሪካዊ የሀገሪቱ ባህል ነው ለማለት ባይደፈርም ለአረመመው ሙሁር መስፍን ወ/ማርያም የሀገሪቱ ባህል ለአገዛዝ የተመቸ መሆኑ አልፎም "እኛ ተጨቋኞች ያልተሳካልን ጨቋኞች" የመሆናችን ሁነት የሀገሪቱን የፖለቲካ ባህል አምባገነናዊ እንዳደረገው እና ወደ ሥልጣን የሚመጡትም መሪዎች አምባገነን የመሆናቸው ፀረ-ምክንያት ማህበረሰባዊ ስለመሆኑ ባቀረቡት ጽሑፍ ተሟግተዋል፡፡

የመለስ ሜታሞርፎሲስ
እንደማንኛቹም ሁኔታዎችና በጠባብ ርዕዮተ-ዓለም አውድ እንደሚንቀሳቀስ የትጥቅ ትግል

ስብሰባ ወያኔ በአመራር ዘዬው እና በትግል አቅጣጫው ላይ ልዩነቶችን ሲያስተናግድ ቆይቷል፡፡ በአስራ ስድስት ዓመቱ የትጥቅ ትግል ጉዞ ፓርቲው ራሱን ከመፈራረስ ቢያድንም ወደ ቀጣዩ እንዲያልፍ ሆኗል፡፡ የ1968ቱን የፓርቲውን ማኒፌስቶ ተከትሎ የመጣው ንትርክ ላይ ብዙ ሲባል ባይሰማም ፓርቲው ራሱን ወደ ምሥራቅ ትግራይ ባስፋፋበት ወቅት ከዚሁ አካባቢ የመጡት አባሎቹ ፓርቲው ከሽሬ፣ አክሱምና አድዋ /በምጽህረ ቃሉ "አአሽ"/ በመጡ ሰዎች አመራሩ በምልዓት መያዙን በመቃወማቸው ከዚህም በመከተል ፓርቲው የተቃውሞ ድምጻቸውን ያሰሙትን በማባረር እና በግድያ ለማፈን መሞከሩ የፓርቲው የመጀመሪያ ስራ ነበር፡፡ ወያኔ ለማጥናት የሚያነሳሳው ብዙም ምቹ ሁኔታ አይገጥመውም፡፡ ፓርቲው በጫካ ትግሉ ወቅትም ሆነ ከዛ ከቀጠሉት ጊዜያት ያጋጠሙትን የውስጥ የሥልጣን ሽኩቻ እና መሰል ክስተቶች ላይ ጥልቅ ትንታኔ የሚሰጡ ድርሳናትም ሆነ አጥኚዎች የሉትም፡፡

ፓርቲው እዚህ ድረስ ዝግ ቢሆንም በዚህ ንዑስ ርዕስ የጠቀስነውን ሁኔታ ጨምሮ ሌሎች ውስጣዊ ሁኔታዎች ብዙም በጥልቀት ባይሆንም ለመዘገብ የሞከሩት ዶ/ር ጆን ያንግ ናቸው፡፡ “Pleasant Revolution in Ethiopia” በሚለው መጽሐፋቸው የፓርቲውን የ16 ዓመት ትግል ጉዞ ጽፈዋል፡፡ ከዚህ በመለስ አልፎ አልፎ ከላይ ከላይ ጉዳዮን ከሚነካኩ ፁሑፎች ውሰጥ “ Two group of TPLF and Two Issues of Ethiopia” በጥቂት ታይቷል፡፡

ህወሓት በ1968 ዓ.ም ሲመሰረት መስራች ከነበሩት የያኔው ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጠባብ በዘር ላይ የተመሰረቱ የትግራይ  ብሔርተኞች እና ግራ ዘመሞች መሀከል የመጀመሪያው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት አቶ አባይ ፀሐዬ፣ ስብሃት ነጋ ፣ አረጋዊ በርሄ፣ ግደይ ዘረጽዮን እና ስዩም መስፍን ሲሆኑ የኮሚቴው ተለዋጭ አባላት ደግሞ መለስ ዜናዊ፣ ስዬ አብርሃ እና አታክልቲ ቀፀላ ነበሩ፡፡ የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት የትግራይ ጠባብ  ብሔርተኞች  ስብስብን በዩኒቨርስቲው አካባቢ የመሰረቱ ሲሆን ሶስቱ ምክትሎቻቸው ደግሞ ከዚህ ስብሰባ በኋላ ወደ ፓርቲው የተቀላቀሉ ታጋዮች ነበሩ፡፡ በእድሜ እና ብሔርተኝነትንም በመረዳት የብሔርተኝነትን እንጂ የኢትዮጵያን ጉዳይ አልነበረም የሚያራምዱት እስከ አስራ ዘጠኝ ሰባ አንዱ የፓርቲው የመጀመሪያ ኮንግረስ በአቶ አረጋዊ በርሄ የፓርቲው ዋና ፀሐፊነት የዘለቀው ህወሐት በዚህ የመጀመሪያው ኮንግረሱ ያሳለፋቸው ሁለት ውሳኔዎች ለመለስ የሥልጣን መሰላልን አስጨበጠ፡፡ የፓርቲው የመጀመሪያ ውሳኔ ፓርቲው ሶሻሊስታዊ ስብስብ የሚሆንበት መንገድ እንዲጠና ማዘዙ ነበር፡፡

ይህን ፓርቲውን ወደ ሶሻሊስታዊ እንቅሰቃሴ የመቀየር ውሳኔ አቶ መለስ እንዲያጠኑ ታዘዙ ለአቶ መለስ ብዙ ዕድሎችን ይዞ መጣ፡፡ ከሚጠሉት የጦርነት አውድማም ራቁ፡፡  ማለትም ጦርነት ይፈሩ ነበር ጊዜያቸውንም ከሌኒን እስከ ስታሊን ከማርክስ እስከ ማኦ ድረስ ያሉትን የግራ ዘመሞቹን የበዙ ሥራዎች በማንበብ አዋሉ፡፡ የፓርቲውን የካድሬ ት/ቤትም በበላይነት መምራት ጀመሩ፡፡ አቶ መለስ ይህን የፓርቲውን ውሳኔ በሚገባ ተጠቅመውበታል፡፡ በዚሁ ኮንግረስ የተላለፈው ሁለተኛው ውሳኔ እስከ ወቅቱ ድረስ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የነበሩት አምስቱ ታጋዮች ወደ ፖሊት ቢሮ አባልነት ሊሻገሩ እና አቶ መለስ ደግሞ ወደ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት አደጉ፡፡ በዚህ ወቅት አቶ መለስ የሚሰሩት የማዕከላዊ ኮሚቴው የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊ አቶ አባይ ፀሐዬ ስር ነበር፡፡

የኮንግረሱን ውሳኔ ተከትሎ ለትጥቅ ትግል በተመሰረተው ህወሓት ውስጥ ከሚሊተሪ ይልቅ ፖለቲካ ትግሉን እንዲወሰን ተደረገ፡፡ ይህን ግንዛቤ ያስገቡት አቶ መለስም በአባይ ፀሐዬ ስር የፓርቲውን ሥልጣን ማጠራቀም ጀመሩ፡፡ የተቀሩትን የፖሊት ቢሮ አባላት አቶ መለስ በአባይ ፀሐዬ በኩል ፖለቲካን የበላይ የሚያደርግ ውሳኔ ማስወሰን ጀመሩ፡፡ በካድሬው ት/ቤትም በኩል አቶ መለስ የት/ቤቱን ካድሬዎች በእርሳቸው ጥላ ስር አሰባሰቡ፡፡ በዚህ መንገድ የቀጠለው የህወሐት እና የመለስ የሥልጣን ዑደት (Power Metamorphosis) ተዛምዶ በ1977 ዓ.ም. ሐምሌ ወር ላይ ማሌሊት ሲመሰረት ለአቶ መለስ እስከዚህ ዘመን ድረስ ለዘለቀው የሥልጣን ጠቅላይነት ጉዟቸው ዋነኛው ምዕራፋቸው ሆነ፡፡ህወሐት

በመጀመሪያው ኮንግረሱ ካሳለፈው ፖለቲካ የበላይነት እንዲኖረው ግድ ከሚለው ውሳኔ በበለጠ መልኩ ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ኦፍ ትግራይ/ማሌሊት/ መመስረት ፓርቲውን ወደ ሙሉ ሶሻሊስታዊ ስብስብነት ቀየረው፡፡ በፓርቲው የበላይ አመራር ውሳኔ የማሌሊት ዋና ፀሐፊ እንዲሆኑ የተመረጡት አቶ አባይ ፀሐዬ ቢሆኑም አሁን በእርሳቸው ሥር በርዕዮተ-ዓለም በመተንተን የመጡት አቶ መለስ ማሌሊትን መምራት ጀመሮ በማሌሊት ሕግጋት መሠረት ማንኛውም የድርጅቱ አባል ማዕከላዊ ኮሚቴውን ሳያስፈቅድ ምንም ዓይነት ሃሳብ ማሰራጨት መከልከሉ ለአቶ መለስ የብቸኛ ሃሳብ አመንጭነትን ማዕረግ ሰጣቸው፡፡ ለዚህም ነው እስከ አሁን ድረስ ህወሓት በትግሉ ወቅት ያሳተማቸው ጽሑፎች ፀሐፊው በግልጽ መታወቅ እንደሌለበት ነው የሚሉት፣ ማለትም አቶ መለስ ለራሳቸው በሚመቻቸው ሁኔታ ነገሮቹን ሁሉ ለማስኬድ ነው፡፡

የማሌሊት መነሻ ፕሮግራም ለህወሐት የመጨረሻ ግቡ ነው፡፡ በ1997 የወጣውና ባለአምስት ገጽ የማሌሊት መግለጫም ፣ ዓላማችን ማኦኢዝምን መሰል ከላሽ አሰተሳሰቦችን መዋጋት እና ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በዓለም ማሰራጨት የሚል አርፍተነገር መያዙ ከጆን ያንግ ድምዳሜ ጋር ያስማማል፡፡ ዋነኞቹ የህወሓት አመራሮች /በተለምዶ የመለስ-ስብሃት ቡድን ተብሎ የሚጠራው/ የማሌሊት አባላት እንደነበሩ ቢዘገብም የማሌሊትን ምስረታ ተከትሎ ከድርጅቱ የተባረሩት አቶ አረጋዊ በርሄ እና ግደይ ዘርዕጽዮን የተባሉት አባላት እንደነበሩ ጆን ያንግ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ አይነኬ በሆነው ማሌሊት በኩል አቶ መለስ በአቶ አባይ በኩል ሊፈጽሙ ያቀዷቸውን ሃሳቦች እየተከራከሩ ያስቸገሯቸውን አረጋዊን እና ግደይን "ለመምታት" እንደቻሉ ይነገራል፡፡ እንደ ጉዳዩ ዘገባ በአቶ መለስ እና አቶ ግደይ መሃከል የርዕዮተ-ዓለም ነው የተባለ 16 ሰዓታት የፈጀ ክርክር ተደረገ፡፡ አቶ መለስ የቀድሞ የትግል ጓዳቸውን "ፖለቲካው ያልገባው የድርጅቱ ጋንግሪን ነው" ሲሉ ተከራከሩ ጋንግሪን ደግሞ ተቆርጦ ካልተጣለ በቀር ሰውነትን እንደሚበክለው ሁሉ ግደይም በድርጅቱ ውስጥ ከቆየ ፓርቲውን እንደሚበክሉ ተነተኑ፡፡ በአቶ አባይ ፀሐዬ መሪነት በተካሄደው በዚህ ስብሰባ አቶ መለስ በካድሬው ት/ቤት በኩል የገሯቸውን ካድሬዎች ለክርክራቸው የአሸናፊነትን ግርማ በጭብጨባ ለገሷቸው፡፡ አቶ ግደይ እና አቶ አረጋዊም ከፓርቲው ተሰናበቱ ከዚህ ክርክር በኋላ አቶ መለስ በፓርቲው ካድሬዎች እና አመራሮች ዘንድ ተደማጭነት አገኘ፡፡በነገራችን ላይ ግደይም ሆነ አረጋዊም ከጠባብ ብሄርተኝነት አልወጡም።

አሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ እንደሚባለው አሁንም ያው ናቸው።የድርጅቱም መዝሙር ማሌሊት ብቻ ሆነ፡፡ እንደ ፓርቲው ታሪክ ማሌሊትን ተንተርሰው ተገዳዳሪዎቻቸውን ከፓርቲው ማራቅ የጀመሩት አቶ መለስ የህወሓት ዋና ፀሐፊነትንም በ1980ዎቹ መጀመሪያ ማሌሊትን በመጠቀም መያዛቸውን ይገልጻሉ፡፡ ዶ/ር ጆን ያንግ በበኩላቸው አቶ ስብሐት ነጋ የመለስን እድሜ እና ሃሳብ መሪነት ጠቅሰው ፓርቲው ወደፊት ለሚጠብቀው ተግዳሮት ሀገሪቱን መምራት ጨምሮ የተሻለ አማራጭ አድርገው ለፓርቲው እንዳቀረቧቸው ጽፈዋል፡፡ስብሐትም ለብዙ ዓመታት በፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት የመቆየታቸውን እና በብዙ የፖለቲካ ታዛቢዎችም ዘንድ እንደ ፓርቲው "የነፍስ አባት" የመቆጠራቸውን ሁነት የሁላችንም አስተያየት የተሻለ ግምገማ መሆኑን ያስረዳናል፡፡ በጋርዮሽ አመራር (Collective leadership) ይመካ የነበረው ህወሐትም ቀስበቀስ ኃይል እያሰባሰቡ በመጡት አቶ መለስ መመራት ጀመረ፡፡ ይህም ሆኖ ግን እስከ 1993ቱ የፓርቲው መፈርከስ ድረስ አቶ መለስ ሥልጣንን በምልዓት ጠቅለው እስኪይዙ ድረሰ የፓርቲው ሰዎች አልጠፉም፡፡ እነርሱም ቢሆኑ ግን ከ1993ቱ ንትርክ በኋላ ከፓርቲው ተሰናብተዋል፡፡

"የቦና ፓርቲዝም ጦስ"
የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን ታኮ የተቀሰቀሰው የሁለቱ የህወሓት ስብስቦች የሥልጣን ትግል

ለአቶ መለስ ምናልባትም የመጨረሻው ትንቅንቅ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከፓርቲው የተሰናበቱት የቀድሞ ታጋዮች (diss-enters) የትንቅንቁን ምክንያት የሀገሪቱ ልዓላዊነት ጥያቄ አድርገው ሲያቀርቡት "የቤተመንግሥቱ" ቡድን በበኩሉ "ሙሰኞች" ነበሩ ሲል ይከሳል፡፡ የሁለቱን ሀገራት ጦርነት ተከትሎ ስለወጣው ይሄ ትንቅንቅ የኢትዮጵያን ወጣት ያስጨፈጨፉት አቶ መለስ ዜናዊ እንደሆኑ በዚህ ጽሑፉ መግቢያ ላይ የተቀስኩት የፕሮፌሰር ጳውሎስ ሚልኪያ ስራ ተጠቃሽ ነው፡፡

የቦና ፓርቲዝምን ጽንሰ ሃሳብ በናፖሊዮን የአጎት ልጅ ሉዌስ ቦና ፓርቲ ስም በመሰየም “18th Brumaire” በሚለው ስራው ካርል ማርክስ ስለሀሳቡ የሰጠው ብያኔ የሚለው በአንድ የመንግሥት አስተዳደር ውስጥ የቡርዣው ማህበረሰባዊ ክፍል የማዕከላዊውን መንግሥት ሥልጣን ሲያጣ እና የሰራተኛው መደብ በበኩሉ ሥልጣኑን ለመያዝ የሙብቃት ደረጃ ላይ ሳይደርስ ሲቀር የሚፈጠር የፖለቲካ አመራር ስልት ነው፡፡ ቦና ፓርቲዝምን መለዩው የሚያደርግም ስርዓት ዋነኛ ግቡ አድርጎ የሚያነሳው የቡርዣውን የማህበረሰብ ክፍል የኢኮኖሚ ብልፅግና ማጠንከር እና ለካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሥርዓት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡ፕሮፌሰር ጳውሎስ እንደሚሉት ለወራት በዘለቀው በዚህ ስብሰባ አቶ መለስ ጽንሰ ሃሳቡን ሲያስረዱ መሠረታዊ ጥልቅ የሆነ ስህተት ሰርተዋል፡፡
ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ ለስብሰባው ባቀረቡት 700 ገጽ ጽሑፍ፣ አንዳንዶቻችሁ የኮሚቴው አባላት ቢስማርክዚምን ለክርክራችን እንድንጠቀም እንዲሆን ብትጠቅሱም ለእኔ ትንታኔ ግን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የተሻለ መንደርደሪያ ነው ማለታቸውን ያስነብቡናል፡፡በዚህ የፓርቲው ውስጣዊ ትግል የእነስዬና ተወልደ ቡድን የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራ የየመን የሀኒሽ ደሴቶችን ስትወር አራት የጦር ሂሊኮፕተሮችን መለገቧን እና የሁለቱ ሀገራትን "ወታደራዊ ስምምነት" በመጥቀስ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጉዳዩ ላይ ማዕከላዊ ኮሚቴው እንዲወያይ ቢጠየቁም አቶ መለስ በበኩላቸው ዋናው ጉዳይ የቦና ፓርቲዝም አመለካከት በመሆኑ ውይይት በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲሆን ተከራከሩ፡፡
ጉዳዩ ወደ ውሳኔ ሲያመራ የነስዬ ቡድን 17 ለ13 በሆነ ድምጽ ቢያሸነፉም አቶ መለስ የውስጥ የቤት ሥራቸውን በሚገባ በመስራታቸው የተቃውሞ ድምፅ ያሰሙት የፓርቲው ልሂቃን አንዳንዶቹ ወደ እስር ቤት ሲወርዱ የተቀሩት ወደ ተቃውሞ ጎራ ተቀላቀሉ፡፡ ፕሮፌሰር ጳውሎስ በወቅቱ አቶ ስብሃት ነጋ ከሌሎች የፓርቲው ሰዎች ጋር ያላቸውን ቤተሰባዊ ዝምድና ፖለቲካዊ ልባስ በመስጠት አቶ መለስን አሸናፊ ሆነው እንዲወጡ እንደዳረጓቸው ተንትነዋል፡፡

እንደ አንዳንድ ተንተኞች ሰውዬውን አሸናፊ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ሌላው ምክንያት ውስጣዊ እና ውጪያዊ ጉዳዮችን ሁሉ ሰለያዙት ነበር፡፡ሀገሪቱን የሚመራ ማንም ሰው የወታደራዊውንም ሆነ የስለላ ክፍሉን የሚያዝበትና የማጭበርበር ልምድ ስላለቸው ሁኔታውን ለውስጣዊ ትግል በማጭበርበር እና በኃይል ሊጠቀሙበት ችለዋል፡፡ ሌላው ወሳኝ ክስተት የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክን ያነበበ ሁሉ እንደሚረዳው ከአፄ ዮሐንስ እስከ ፋሺስት መንግሥቱ እና አቶ መለስ ያሉ መሪዎች የሥልጣን ተገዳዳሪዎቻቸውን በአደባባይ ለማስወገድ ሲጠቀሙበት የነበረው የሌሎች ሀገራትን /በተለይም የምዕራባውያንን/ በሀገሪቷ ውስጥ ያላቸውን ፍላጎት የኢትዮጵያን ሕዝብ በማሰቃየት/በመጨቆን ከሥልጣን እስከ ሞት ድረስ በመጠቀም የጭካኔ ራዕያቸውን አስተላልፈው አልፈዋል።

የኢትዮጵያን ሕዝብ እየዋሸና እያጭበረበሩ የፖለቲካ ሂደቱ በጥሩ ሁኔታ እየሄደነው የሚሉት አቶ መለስ ለምዕራባውያኑ ራሳቸውን "የነጻ ገበያ አራማጅ" አድርገው ሲያቀርቡ ተቀናቀኞቻቸውን ደግሞ፣ ጠባብ የትግራይ ብሔርተኞች፣ እንደሆኑ ለማሳመን ሞከሩ፡፡ አቶ መለስ የወታደራዊውንም ሆነ የስለላ ክፍሉ የገጠማቸውን ማዕበል አልፈው ሥልጣናቸውን በዙሪያቸው ከአደላደሉ በኋላ ማንኛውንም ነገር ማድረግ ጀመሩ፡፡ በእርግጥ ህወሓት ለሁለት ሳይከፈልም የእሳቸው ትዕዛዛዝ ተሰሚነት ነበረው፡፡

ለምሳሌ በማዕከላዊ እስር ቤት ለ 14 ዓመታት እንደቤታቸው አድርገው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያሰቃዩ እና ሲገርፉ የነበሩት እነ ታደሰ መሰረት፣ ፀሐዬ ካሕሳዬ፣ ተወልደ፣ ፀጋዬ ወዘተ የነበሩት አሁን በስራ ላይ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ በሌላ ቦታ ተቀይረው ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም በ 1994 ዓ.ም የቤተ መንግሥት ደህንነት ጥበቃ በኃላፊነት ሲመሩ የቆዩት አቶ ዘርዑ መለስ በወቅቱ ከአቶ መለስ ጋር ባለመስማማት "ሚልክሃውስ" 1ኛ ፎቅ ቤታቸው ውስጥ አንገታቸው ታርዶ ነው የተገኙት ግድያውን የፈፀመው ወ/ሥላሴ ወ/ሚካኤል የሚባለው ደህንነት ሹም ነው፡፡እንደዚሁም በአቶ መለስ የተሾሙት ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሥላሴ ለማንኛውንም ነገር ፈላጭ ቆራጭ ነበሩ፡፡ ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ አሁንም በሥልጣን ላይ ናቸው፡፡ ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ ከስብሃት ነጋ እና ከመለስ ጋር ዝምድና አላቸው፡፡ እንደዚሁም በግፍ የተገደሉት የመገናኛ ሚኒስትር አቶ አያነውና እንዲገደሉ ያደረጓቸው አቶ ኢሳያስ እና ወ/ሥላሴ ናቸው፡፡ በ 1997 በሰላማዊው ሰው ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ያደረጉ እንደነዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ማነቆዎች ናቸው፡፡ ሥልጣንን መከታ በማድረግ፡፡
የታሪክ ሸክም

እኔ በጣም ከሚገርመኝ ሁሉ አቶ መለስ ይጠቀሙበት የነበረች አንድ ብሂል ነበረቻቸው "አፍሪካ ስማቸው በ"M" የሚጀምር ሁለት አምባገነኖች እና ጨቋኞች አይታለች ፋሽስቱ መንግስቱ ኃይለማርያም እና ሞብቱ ሴሴኮ፡፡ በእነርሱ ላይ ሶስተኛ "M" መጨመር አልፈልግም ይሉ ነበር እኔ ግን እንዲህ ይመስለኛል፡፡"ብእሲ ነባቢ ኢያረትእ በዲ በምድር " "ወለብእሲ ዐማዒ ትንዕዎ እኪት ለአማስኖ" ይላል መቀባጠርን የሚያበዛ ሰው አንድም አገሩን አንድም መንግሥቱን አያቀናም፡፡ዓመፀኛን ሰው ክፋት ለጥፋት ይፈልገዋል።

አሁን እዚህ ላይ እንደተጠቀሰው እንደ ሁለቱ መሪዎች ሥልጣን ይዘው ነበር፡፡ በሁለቱም የበለጠ ሆነው ተገኝተው ነበር፡፡ በህወሓት የመሪዎች ስብስብ ውስጥ የትግል ዘመን እኩዮቻቸው በሞት እና በእስር ሸኝተው ነበር፡፡ አቶ መለስም አልቀረላቸውም የራሳቸው በደል አሰናብቷቸዋል። አቶ መለስ እንደደረሱበት ሥልጣንን የጠቀለሉበትን ጥግ ፋሽስቱ መንግሥቱም በሥርዓታቸው ዘመን ማምሻ ወቅት ደርሰውበት እንደነበር ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ “The Burden of history” በሚለው ሥራቸው ጽፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ የአምባገነንነትን የጭካኔ ፖለቲካ ባህል ከሀገሪቱ የፖለቲካ ተሞክሮ እንደሚነሳ የሚናገሩት ፕ/ሩ ሁኔታውን፣ የታሪክ ሸክም ሲሉ ጠርተውታል፡፡ ከ 1983 ጀምሮ አቶ መለስ የሀገሪቱን የፖለቲካ ባህል በሃሳባቸው ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ እንደሚፈልጉ ለዚህም በርትተው እንደሚሰሩ ሲናገሩ ነበር፡፡ አቶ መለስ ዓላማቸው ለካ የአገዛዝ ዘመናቸው ግን ወደ ብቻ መሪነት (Strong man) መቀየራቸውን እንደሚያሳይ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ይስማማሉ፡፡ እንደተንታኞቹ አቶ መለስ በዚህ የሥልጣን ጠቅላይነት የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥፋት የመጡ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የታሪክ ሸክም ይሏቸዋል፡፡ የፕሮፌሰር ባህሩ ክርክር ይቅርታ አያሰጣቸውም፡፡

የታሪክ መምህራን እንደሚሉት "ከታሪክ ያልተማረ" አገር አጥፊ ይባላል፡፡ እኔም በበኩሌ "ምንተ ንግበር አኃዊነ" "ወንድሞቻችን ምን እናድርግ" እላለሁ፡፡ሌላው የአሁኑ ጠ/ር ኃይለማሪያም ደሳለኝ ራዕይ አስፈፃሚ ልበለው ወይስ ጉዳይ አስፈፃሚ እኔ አሁንም የሚመስለኝ መለስ መልኩ ተለወጠ እንጂ አልሞተም ያስብላል።

የሰው ልጅ አዕምሮን የሚያክል ፍጡር እያለው ያውም ደግሞ ተምሪያለሁ የሚል በሄደበት የሳቸውን ራዕይ ጥግ ማድረስ ነው እንዳለ ከእውነት እንደራቀ ይኸው የ 2007 ምርጫ ሊመጣበት ነው።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ስልጣን ለሁለት ተከፍሏል። የኤርትራን ኢንተረስት የሚያስጠብቅ እና የትግራይን ኢንተረስት የሚያስጠብቁ ናቸው።ሀገር እየመራ ያለው ኃይል ለሁለት የተከፈለ ቢሆንም፣ በአንፃራዊነት በጥምር የሚሰራ መሆኑን ነው፡፡የእነዚህ ሁለት ቡድኖች

የጉልበት ምንጭም የታጠቀውን ኃይል በመቆጣጠር እና የፖለቲካውን ሥልጣን በመያዝ ላይ የተመሰረተ ነው፤ ይኸውም ሠራዊቱ እና የደህንነት መስሪያ ቤቱ ሙሉ በሙሉ በህወሓት ሰዎች ሲንቀሳቀሱ፣ ፖለቲካውን ደግሞ የብአዴን መሪዎች፣ ከተወሰኑ የኦህዴድና ደህአዴን የአመራር አባላት ጋር ተባብረው መያዛቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች መኖራቸው ነው፡፡

በህወሓት ውስጥ ብዙ የስልጣን ሹኩቻዎች እንዳሉ የታወቀ ቢሆንም ዶ/ር ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል እና ጌታቸው አሰፋ የተሰለፉበት ቡድን ተፅእኖ ፈጣሪ ሆኖ መውጣት ችሏል፤ ይህም ሆኖ ውስጥ ውስጡን ተንኮልም ሆነ ሽኩቻ ገና መቋጫ አለማግኘቱ ግልፅ ነው፡፡ በዚህ ላይ የማነሳቸው በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩኝም በቅድሚያ መጠየቅ የምፈልገው ጥያቄ ቢኖር ለመሆኑ ጠ/ሚ/ር ሃይለማርያም ደሳለኝ እስከመቼ ድረስ ነው ራዕይ አስፈፃሚነቱ የሚያበቃው?ህወሓት ሆነ አቶ ሃይለማርያም የህዝብ ውክልና ያላቸው ባይሆኑም የሥራ አስፈጻሚው ሥልጣን የተሰጠው ለእርሳቸው በመሆኑ በዚህ ጊዜ የመለስን ራዕይ አስፈፃሚነት ሳይሆን በግልጽ በመታየት የሥራ አስፈጻሚነት ተግባራቸውን መወጣት ይገባቸው እንደነበር የእኔ ብቻ ሳይሆን የበርካታ ኢትዮጵያውያን ጥያቄ ነው።

እንደዚያም ሆኖ ግን አሁንም አቶ ኃይለማርያም ከአቶ መለስ በተለየ መልኩ አዎንታዊ ለዉጦች ሊያመጡ ይችላሉ የሚል ተስፋ የለኝም። ይሄንንም ስል ያለ ምክንያት አይደለም።ምንም ማምጣት ስለማይችሉ።በሌላ በኩል ደግሞ በፓርቲውም ሆነ በመንግስት አስተዳደር ከህወሓት ሰዎች ትልቁን ስልጣን የያዘው ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል ይባላል።ለጊዜው ጽሑፌን በዚህ ልቋጨውና በሌላ ጊዜ በሰፊው እመለስበታለሁ ቸር እንሰንብት።

አሜን! እግዚአብሔር ኢትዮጵያ አገራችንን ይጠብቅልን፡፡

ዳዊት ተመስገን